የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ህዳር ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.12
ADDIS ABABA 9th December , 2015

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ .....ገጽ ፰ሺ፭፻፹፪

Proclamation No. 916./2015
Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation -------------Page 8582

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንናተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት ስልጣንናተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል::

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

Proclamation No. 916./2015

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

WHEREAS, it has been found necessary to redefine the Organization, Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015”.

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል::

**ክፍል ሁለት**
**ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት**

**፫. ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣና ተግባር**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣንና ተግባር በሕገ መንግሰቱ አንቀፅ ፸፬ የተመለከተው ይሆናል ::

**፬. ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣና ተግባር**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣንና ተግባር በሕገ መንግሰቱ አንቀፅ ፸፭ የተመለከተው ይሆናል ::

**፭.ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር በሕገ መንግሰቱ አንቀፅ ፸፯ የተመለከተው ይሆናል::

**፮. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከለተሉት አባላት ይኖሩታል፦

**2. Definition**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "Regional State" means any State referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city Administrations;

2/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**PART TWO**
**THE PRIME MINISTER, THE DEPUTY PRIME MINISTER AND THE COUNCIL OF MINISTERS**

**3. Powers and Duties of the Prime Minister**

The powers and duties of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 74 of the Constitution.

**4. Powers and Duties of the Deputy Prime Minister**

The powers and duties of the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 75 of the Constitution.

**5. Powers and Duties of the Council of Ministers**

The powers and duties of the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 77 of the Constitution.

**6. Members of the Council of Ministers**

1/ The Council of Ministers shall have the following members:

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፤

ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፱ የተመለከቱትን ሚኒስቴሮች የሚመሩ ሚኒስትሮች፤ እና

መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣኖች::

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩(ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታዎች በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋሉ::

ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል::

**፯. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ስነ ስርዓት</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡-

ሀ) የራሱ የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወስነው መሰረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ያደርጋል፤

ሐ) ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፤

መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምፅ ይሆናል፣በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል::

፪/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡-

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

a) the Prime Minister;

b) the Deputy Prime Minister;

c) Ministers heading the ministries specified under Article 9 of this Proclamation; and

d) other Officials to be designated by the Prime Minister.

2/ Where any Minister referred to in sub-article 1(c) of this Article cannot attend the meeting of the Council, the Minister of State of the Ministry shall take part in the meeting of the Council. Where there are more than one Ministers of State unless specific delegation has been given by the Minister, the senior Minister of State shall, take part in the meeting of the Council.

**7. <u>Meeting Procedure of the Council of Ministers</u>**

1/ The Council of Ministers shall:

a) have its own procedural manuals;

b) conduct ordinary and extraordinary meetings in accordance with its rules of procedure;

c) have a quorum where more than half of its members are present;

d) pass decisions by consensus or, failing that, by majority vote.

2/ The Prime Minister shall:

a) without prejudice to the rights of the members of the Council of Ministers to propose agenda items, determine the agenda of the Council;

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል::

፫/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል::

፰. **የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል::

፪/ የቋሚ ኮሚቴዎች ስልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል::

## ክፍል ሶስት
## ስለሚኒስቴሮች

፱. **መቋቋም**

የሚከተሉት ሚኒስቴሮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

፩/ የአገርመከላከያ ሚኒስቴር፤

፪/ የፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር፤

፫/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤

፬/ የፍትሕ ሚኒስቴር፤

፭/ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር፤

፮/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፤

b) preside over the meetings of the Council;

c) adjourn the meetings of the Council under circumstances where he finds it necessary to refer a case included in the Council's agenda to the relevant Committee of the Council.

3/ In the absence of the Prime Minister, the Deputy Prime Minister shall preside over the meetings of the Council.

8. **Standing Committees of the Council**

1/ The Council of Ministers may, with a view to facilitating its functions, have various standing committees comprising of its members.

2/ The powers and duties of standing committees shall be defined in the manuals of the Council.

## PART THREE
## MINISTRIES

9. **Establishment**

The following Ministries are hereby established:

1/ the Ministry of National Defense;

2/ the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs;

3/ the Ministry of Foreign Affairs;

4/ the Ministry of Justice;

5/ the Ministry of Public Service and Human Resource Development;

6/ the Ministry of Finance and Economic Cooperation;

፯/ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፤

፰/ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር፤

፱/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤

፲/ የንግድ ሚኒስቴር፤

፲፩/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤

፲፪/ የትራንስፖርት ሚኒስቴር፤

፲፫/ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤

፲፬/ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፤

፲፭/ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፤

፲፮/ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፤

፲፯/ የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር፤

፲፰/የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፤

፲፱/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር፤

፳/ የትምህርት ሚኒስቴር፤

፳፩/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤

፳፪/ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒቴር፤

፳፫/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤

፳፬/ የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፤

፳፭/ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፡፡

7/ the Ministry of Agriculture and Natural Resources;

8/ the Ministry of Livestock and Fisheries;

9/ the Ministry of Industry;

10/ the Ministry of Trade;

11/ the Ministry of Science and Technology;

12/ the Ministry of Transport;

13/ the Ministry of Communications and Information Technology;

14/ the Ministry of Urban Development and Housing;

15/ the Ministry of Construction;

16/ the Ministry of Water, Irrigation and Electricity;

17/ the Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas;

18/ the Ministry of Environment, Forest and Climate Change;

19/ the Ministry of Public Enterprises;

20/ the Ministry of Education;

21/ the Ministry of Health;

22 / the Ministry of Labour and Social Affairs;

23/ the Ministry of Culture and Tourism;

24/ the Ministry of Women and Children Affairs;

25/ the Ministry of Youth and Sports.

## ፲. የሚኒስትሮች የወል ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ሚኒስቴር፡-

፩/ በሥራው መስክ፡-

ሀ) ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌደራል መንግሥቱ ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፣ መረጃዎችንይሰበስባል፣ያቀነባብራል፣ያሰራጫል፤ ብራል፣ያሰራጫል፤

መ) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ዉጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) ለክልሎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በፌደራል ጉዳዮችና የአርብቶ አደር ልማት ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፤

፪/ በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞ ቻቸውንና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፤

## 10. Common Powers and Duties of Ministries

Each Ministry shall have the powers and duties to:

1/ in its area of jurisdiction:

a) initiate policies and laws, prepare plans and budgets, and upon approval implement same;

b) ensure the enforcement of federal laws;

c) undertake study and research; collect, compile and disseminate information;

d) undertake capacity building activities; implement, cause to implement and ensure effectiveness of the reform and good governance works;

e) provide assistance and advice to Regional States, as necessary; and provide coordinated support to Regional States eligible for affirmative support as coordinated by the Ministry of Federal Affairs and Pastoralist Development;

f) enter into contracts and international agreements in accordance with the law;

2/ direct and coordinate the performances of the executive organs made accountable to it under the laws establishing them or under Article 38 of this Proclamation; review the organizational structures as well as the work programs and budgets of the executive organs and approve their submission to the appropriate government organs;

፫/ የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፬/ የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያለባቸው ሰዎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፭/ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

፮/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፯/ ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ፲፩. የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

፩/ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

፪/ የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

፫/ ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

3/ address women and youth affairs in the preparation of policies, laws and development programs and projects;

4/ create, within its powers, conditions whereby persons with disabilities, the elderly, segments of society vulnerable to social and economic problems and H.I.V. AIDS positive citizens benefit from equal opportunities and full participation;

5/ exercise the powers and duties given to it under this Proclamation and other laws;

6/ where necessary, delegate part of its powers and duties to other federal or regional state organ;

7/ submit periodic performance reports to the Prime Minister and the Council of Ministers.

## 11. Accountability and Responsibility of Ministers

Each Minister shall:

1/ be accountable to the Prime Minister and the Council of Ministers;

2/ represent and exercise the powers and duties of the Ministry he is heading;

3/ effect payments in accordance with the budget and work programs approved for the Ministry;

፬/ በሚኒስቴሩ ውስጥ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

4/ ensure the implementation of performance management system within the Ministry.

## ፲፪/ የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩/ የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል

፪/ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፡፡ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል፡፡

## 12. Accountability and Responsibility of Ministers of State

1/ Each Minister of State of a Ministry shall be accountable to the Minister and shall carry out the responsibilities specifically entrusted to him.

2/ The Minister of State shall act on behalf of the Minister in his absence. Where there are more than one Ministers of State the senior Minister of State shall act on behalf of the Minister in his absence.

## ፲፫/ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት ያስከብራል፤

፪/ መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤

፫/ የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ መሆኑንና ተግባሩንም ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

፬/ የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

## 13. The Ministry of National Defense

The Ministry of National Defense shall have the powers and duties to:

1/ defend the territorial integrity of the country in cooperation with the appropriate organs;

2/ establish, equip and supervise the defense forces and ensure their combat capabilities;

3/ ensure that the composition of the national defense forces reflect equitable representation of nations, nationalities and peoples and that they carry out their functions free of any partisanship to any political organization;

4/ organize training center establishments for the defense forces;

፭/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም ወይም ማናቸውም ክልል ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥል በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤

፮/ የሽምቅ ውጊያንና ሽብርተኝነትን ይከላከላል፤

፯/ የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፤ያሠራል፤

፰/ በክተት ጊዜ በአገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ አያጠና ያስወስናል፤

፱/ የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፤ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲/ በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፤እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ ዕገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፤ ያሰለጥናል፤ያደራጃል፤

፲፩/ ሀገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌደራልና የክልል አካላት ያስተባብራል፤በመተባበርም ይሠራል፤

፲፪/ ሀገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሠላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፤ያሰማራል፤

5/ enforce security measures and the constitutional order, when instructed in accordance with the provisions of the Constitution, where situations endangering public safety are beyond the control of Regional States or where any Regional State violates the Constitution and endangers the constitutional order;

6/ combat guerrilla and terrorist activities;

7/ construct and cause the construction of military camps and residential quarters required for the defense forces;

8/ prepare plans and get authorizations for the coordinated utilization of resources in the country that may be required in an event of national mobilization;

9/ prepare schemes whereby the public can defend or guard itself against enemy threats when general mobilization is declared; and, upon authorization, implement same in cooperation with concerned organs;

10/ recruit, train and organize National reserve force that shall join the armed forces in time of war or state of emergency and that shall provide assistance in the event of man-made or natural disasters;

11/ coordinate the activities of, and cooperate with the appropriate Federal and Regional State organs in matters relating to the defense of the country;

12/ organize and deploy competent peacekeeping forces where the country is required to participate in international peacekeeping missions;

፲፫/ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኘውን ገቢ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለሀገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፡-

ሀ) የመከላከያ ተቋማት በሠላም ጊዜ የሚኖራ ቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም ለገቢ ማስገኛ ተግባር እንዲውል በማድረግ የሚገኘውን ገቢ፤

ለ) ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረ ቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ፤እና

ሐ) በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ፤

፲፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፫) የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል፤

፲፭/ የሠራዊቱ አባላት በሠላም ጊዜ በአገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

**፲፬. <u>የፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>**

፩/ የፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

13/ retain and utilize, for capacity building of National defense upon obtaining the approval of the Council of Ministers:

a) revenue generated by engaging idle facilities of defense institutions, in peace times, in income generating activities;

b) the proceeds of disposal of properties which are no more required for defense purposes; and

c) dividends from enterprises put under its supervision;

for national defense capacity building projects.

14/ ensure that the procedures and standards embodied in the Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and, regulations and directives issued pursuant to the Proclamation are followed in the administration of the fund referred to in sub-article (13) of this Article and submit same for auditing by the Auditor General;

15/ ensure that the defense forces participate in the country's development activities in times of peace.

**14. <u>The Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs</u>**

1/ The Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs shall have the powers and duties to:

ሀ) የሕዝቡ ሠላም መጠበቁን በማረጋገጥ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

ለ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ እና ፷፪ (፮) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

ሐ) አግባብ ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን ፖለቲካዊ መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ፌደራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

ሠ) በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌደራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

ረ) ለክልሎች በተለይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፤

ሰ) ሌሎች የፌደራል መንግሥት አካላት ለአርብቶ አደሩና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚያደርጓቸውን ድጋፎች ያስተ ባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

a) cooperate with concerned Federal and Regional State organs in maintaining public order;

b) without prejudice to the provisions of Article 48 and 62(6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, facilitate the resolution of disputes arising between Regional States;

c) without prejudice to the provisions of the relevant laws and upon requests of Regional States, devise and implement sustainable political solutions for disputes and conflicts that may arise within Regional States;

d) coordinate the implementation of decisions authorizing the intervention of the Federal Government in the affairs of Regional States;

e) serve as a focal point in creating good Federal-Regional relationship and cooperation based on mutual understanding and partnership and thereby strengthen the Federal system;

f) provide assistance to Regional States particularly to those deserving special support;

g) coordinate, integrate and follow up supports given by other Federal Organs to pastoralists and Regional States deserving special support;

ሸ) በተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች መካከል ሠላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣የሃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸውም አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤ የሃይማኖት ድርጅቶችንና ማኅበራትን ይመዘግባል፤

ቀ) በኃይማኖት ሽፋን የሚደረግ አክራሪነትና ጽንፈኛነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ያስፈጽማል፤

በ) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽንና የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያጋግጣል፤

ተ) የጦር መሣሪያ፣የተኩስ መሣሪያ ወይም ፈንጂ ለመያዝ ወይም በእነዚሁ ለመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፣ፈንጂ ስለሚሸጥበት ሁኔታ ይወስናል፣ ፈንጂ ለሚሸጡና የጦር ወይም የተኩስ መሣሪያ ለሚያድሱ ፈቃድ ይሰጣል፤

ቸ) በፌደራል ደረጃ የሚከናወኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማኅበራት ምዝገባ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋጋጣል፤

ኀ) በአርብቶ አደር አካባቢዎች ድህነትን ለመቀነስ እንዲሁም የድርቅ ተጋላጭነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል፤

h) work in collaboration with pertinent Government Organs, Religious Institutions and other organs to ensure that peace and mutual respect will prevail among followers of different religions and beliefs, and to enable the prevention of conflicts; register religious organizations and associations;

i) devise and enforce strategies for combating extremism and radicalism committed under the disguise of religion;

j) ensure the proper execution of functions relating to Federal Police Commission and Federal Prisons Administration;

k) issue permit for the possession or use of arms, firearms and explosives; determine conditions applicable for the selling of explosives; issue permits for the selling of explosives and repairing of arms and fire arms;

l) ensure the proper execution, at the federal level, of functions relating to the registration of charities and societies;

m) in collaboration with concerned organs coordinate activities carried out in pastoralist areas to reduce poverty as well as to avoid draught vulnerability;

ነ) አርብቶ አደሮችን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያስተባብራል::

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

n) in collaboration with concerned organs coordinate activities that enable pastoralists to become beneficiaries of social and economic developments.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Federal Affairs by the provisions of other laws, currently in force, are hereby given to the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs.

## ፲፭. የውጨ ጉዳይ ሚኒስቴር

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

፩/ ሀገሪቱ በሚኖራት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤

፪/ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፫/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤እንዲሁም ሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

፬/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

## 15. The Ministry of Foreign Affairs

The Ministry of Foreign Affairs shall have the powers and duties to:

1/ safeguard the interests and rights of the country in connection with its foreign relations and ensure that they are respected by foreign states;

2/ ensure that the country's good relations with neighboring countries are strengthened;

3/ in consultation with the concerned organs negotiate and sign, upon approval by the Government, treaties that Ethiopia enters into with other States and International Organizations, except in so far as such power is specifically given by law to other organs; and effect all formalities of ratification of treaties;

4/ ensure the enforcement of rights and obligations arising from treaties signed by the Ethiopian Government except in so far as specific power has legally been entrusted to other organs;

፭/ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ውሎች ሁሉንም የተመሰከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤

፮/ የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

፯/ በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

፰/ ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግስታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

፱/ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሃገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለምአቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲/ በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

፲፩/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፡፡

5/ register and keep all authentic copies of treaties concluded between Ethiopia and other States and International Organizations;

6/ perform the functions of a depository of multilateral treaties when the Ethiopian Government is a depository of such treaties;

7/ coordinate and supervise the activities of Ethiopia's diplomatic and consular missions and permanent missions of Ethiopia to international organizations;

8/ coordinate all relations of other Government Organs with Foreign States and international organizations;

9/ keep contacts, as may be necessary, with foreign diplomatic and consular representatives in Ethiopia as well as with representatives of International Organizations with a view to facilitating the protection of mutual interests;

10/ ensure that privileges and immunities accorded to foreign diplomatic missions and representatives of international organizations under international laws and treaties to which Ethiopia is a party are respected;

11/ issue diplomatic and service passports and diplomatic and service entry visas in accordance with the relevant laws;

፲፪/ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ፡-

ሀ) የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም በማስፋፋት፣

ለ) የውጭ ኢንቨስትሮችን በመለየትና በመሳብ፣

ሐ) ቴክኖሎጂን በማፈላለግ፣ በመምረጥ እና በማስገባት፣

መ) የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ፣

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

፲፫/ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፬/ የዲያስፖራ ተሳትፎን በማረጋገጥ ዲያስፖራው በአገር ልማት እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፲፭/ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፲፮/ በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የአገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸ ውን ይከታተላል፡፡

**፲፮. <u>የፍትህ ሚኒስቴር</u>**

የፍትሕ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የፌደራል መንግሥት ዋና አማካሪ ሆኖ ይሠራል፤



12/ through pursuing economic diplomacy, cooperate with the concerned organs in:

a) promoting the country's foreign trade and tourism;

b) identifying and attracting foreign investors;

c) identifying, acquiring and packaging of technologies;

d) facilitating the mobilization of external financial and technical assistances;

13/ ensure that the interests and the rights of Ethiopians residing abroad are protected; encourage and support associations formed by Ethiopian communities and friends of Ethiopia;

14/ facilitate participation of the diasporas in the development of the country through ensuring diasporas engagement;

15/ provide information and consultancy on issues of protocol;

16/ design and follow up the implementation of public diplomacy and communication strategies to build the country's image and to rally supporters.

**16. <u>The Ministry of Justice</u>**

The Ministry of Justice shall have the powers and duties to:

1/ be chief advisor to the Federal Government on matters of law;

፪/ የሕግ ማሻሻያና ለፍትህ ሥርዓቱ ጠቃሚነት ያላቸው ጥናቶችን እንዲሁም የኮዲፊኬሽን የፌደራል ሕጎችን የማጠቃለል ሥራ ያካሂዳል፣ የክልሎችን ሕጎች ያሰባስባል፣ እንደአስፈላጊነቱም እንዲጠቃለሉ ያደርጋል፤

፫/ በፌደራል መንግሥት አካላትና በክልሎች ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆች በማዘጋጀት ይረዳል፤

፬/ የወንጀል መነሻዎችን ያጠናል፣ ወንጀል የሚቀንስበትን ሥልት ይቀይሳል፤ በወንጀል መከላከል ረገድ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ አካላትና ኅብረተሰቡን ያስተባብራል፤

፭/ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የምርመራ ሂደቱን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ የጥፋተኝነት ድርድር ይፈቅዳል፣ ይደራደራል፤ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረን ምርመራ ያቋርጣል ወይም ተጨማሪ ምርመራ ያከናውናል፤

፮/ የፌደራል መንግሥትን በመወከል የወንጀል ክስ ይመሠርታል፣ ይከራከራል፤ በቂ ምክንያት ሲኖር በሕግ መሠረት ክሱን ያነሳል፤ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

፯/ የወንጀል ፍትህ መረጃዎች አሰባሰብ፣አያያዝና ሥርጭት ሥርዓት ይዘረጋል፤ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ድጋፍ ይሰጣል፤

2/ undertake legal reform and studies that have importance for the justice system and carry out the codification and consolidation of federal laws; collect Regional State laws and consolidate same as may be necessary;

3/ assist in the preparation of draft laws when so requested by Federal Government Organs and Regional States;

4/ study the causes of crimes; devise ways and means of crime prevention; coordinate the relevant Government Organs and Communities in crime prevention;

5/ undertake or order the conduct of investigation where it believes that a crime the adjudication of which falls under the jurisdiction of the Federal Courts has been committed; direct and supervise the process of the investigation; allow and negotiate plea-bargain; upon the existence of good cause, decide on the discontinuance of an investigation or the carrying out of additional investigation;

6/ represent the Federal Government in the institution and trial of criminal charges; withdraw criminal charges for good causes and in accordance with the law; follow up the execution of decisions of the courts;

7/ establish systems for gathering, handling and distribution of information relating to criminal justice; and provide support to the concerned organs of justice;

፰/ የሕዝቡን እንዲሁም የፌደራል መንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የፌደራል መንግስትን መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች፦

ሀ) ተከራካሪ በሆኑባቸው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች እነዚህን ተቋማት በመወከል ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም የክርክር ደረጃ ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤ የፍርድ ባለመብት የሆኑባቸውን የፍርድ ቤት ውሳኔዎችም እንዲፈጸሙ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ለ) ለሚገቧቸው የውል ግዴታዎች የሚያዘጋጁትን ረቂቅ የውል ስምምነት በመገምገም የሕግ ምክር ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም ረቂቅ ውል ያዘጋጃል፤

፱/ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ተከራካሪ የሚሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክሶችና የመብት ጥያቄዎች አያያዝን ይከታተላል፣ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ ብቃት ያለው የሕግ ባለሙያ መመደቡን ያረጋግጣል፣ የሕግ ጥሰት አለ ብሎ ሲያምን የእርምት መመሪያ ይሰጣል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፤

8/ where the rights and interests of the public and of the Federal Government so require:

a) institute suit civil suits on behalf of federal government offices and public enterprises or intervene at any stage of the proceedings of such suit before the competent courts or other judicial bodies; and follow up the execution of court decisions which made them judgment creditors;

b) review and provide legal advice to the federal government offices and public enterprises when they are entering contractual obligation or in preparing draft contract document and; prepare draft contract document as may be necessary;

9/ follow up, as necessary, the handling of civil suits and claims to which the Federal Government offices and Public Enterprises are parties; cause reports to be submitted to it on same, and ensure that competent legal professionals are assigned; where it believes that an infringement of the law has been committed, it shall give instructions to rectify the irregularities and follow up the observance of same;

፲/ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች እርስ በርሳቸው ተከራካሪ ወገን የሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክርክሮችን በድርድር እንዲያልቁ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፩/ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችንና ሕፃናትን ወክሎ ይከራከራል፤

፲፪/ በፌደራል ፍርድ ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች በሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤ ጠበቆች ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ለመንግስትና ለህዝብ ስለሚሰጡበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ ግዴታቸውንም እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል፤

፲፫/ የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በሕግ መሠረት ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፬/ በወንጀል ጉዳዮች የዓለም አቀፍ ትብብርን በሚመለከት የሚፈጸሙ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

፲፭/ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን አለም ዓቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ለሚነሱ ጉዳዮች አግባብ ያለው ምላሽ ይሰጣል፤ የስምምነቶቹን ብሔራዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፤

፲፮/ ነፃ የሕግ ድጋፍን በተመለከተ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፤

10/ assist in the amicable resolution of disputes arising between federal government offices and public enterprises;

11/ represent citizens, in particular women and children, who are unable to institute and pursue their civil suits before the federal courts;

12/ license and supervise in accordance with law the advocates practicing before federal courts; facilitate conditions necessary for the advocate to provide free legal aid service to the Government and the public, and supervise execution of such obligation;

13/ ensure that whistleblowers and witnesses of criminal offences are accorded protection in accordance with the law;

14/ coordinate activities involving international cooperation with respect to criminal cases;

15/ follow up the implementation of international and regional human rights agreements ratified by Ethiopia; in collaboration with concerned organs give appropriate response to issues raised and prepare national report on the implementation of the agreements;

16/ design strategies for the provision of free legal aid service; follow up its implementation; coordinate those involve in the field;

፲፯/ ብሔራዊ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፰/ ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የሕዝብን ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግ ትምህርት ይሰጣል፤ የሕግ ትምህርትንና ሥልጠናን በሚመለከት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፡፡

፲፱/ በፌዴራል ደረጃ ልዩ ልዩ አካላትን በማስተባበር የተቀናጀ የንቃተ ሕግ መርሀ-ግብር በየዓመቱ ያወጣል፣ ከሕገ-መንግስት፣ ከሰብአዊ መብት አጠባበቅና ሌሎች ልዩ ልዩ ሕጎች አንፃር የንቃተ ሕግ ትምህርትን ለህብረተሰቡ ይሰጣል፣ በልዩ ልዩ አካላት የሚሰጥ የንቃተ ሕግ ትምህርት ሕገ-መንግስቱንና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማስከበር የሚረዳ መሆኑን ይከታተላል፣ ሥልጠናን በሚመለከት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፡፡

**፲፯. <u>የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር</u>**

፩/ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፤

17/ prepare national human rights action plan in cooperation with the concerned organs; follow up its implementation; coordinate the concerned organs at national level and submit report;

18/ create legal awareness through the use of various methods with a view to raising public consciousness in relation to the protection of human rights; cooperate with the appropriate bodies in providing legal education and training;

19/ prepare structured legal awareness creation action plan by coordinating different organs at federal level; provide legal awareness creation training to the public on the constitutional issues, protection of human rights and different laws; follow up the significance of trainings provided by different organs for the respect of the constitution and the constitutional order.

**17. <u>The Ministry of Public Service and Human Resource Development</u>**

1/ The Ministry of Public Service and Human Resource Development shall have the powers and duties to:

a) adopt strategies for continuous human resource development and deployment activities of executive organs, public enterprises and private sectors of the country;

ለ) ብቃት ያለው፣ ውጤታማና ልማታዊ አመለካከት ያለው አመራርና ፐብሊክ ሰርቪስ እንዲገነባ ስልት ይቀይሳል፣ የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሐ) በሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በክትትልና ድጋፍ አግባብ ያስተባብራል፤

መ) ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ መንግስትን፣ ሕዝብንና ልማታዊውን ባለሀብት አቀናጅቶ በሠራዊት አግባብ ያስተባብራል፤

ሠ) የፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደርጋል፤

ረ) የፐብሊክ ሰርቪሱ በብቃትና በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፣

ሰ) የፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ስነምግባር መከታተያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ) የፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች አስተዳደር ሕጎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

ቀ) የመንግሥት ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያስተባብራል፤ የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ በቀጣይነት የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

b) adopt strategies for building competent, effective and development oriented leadership and public service; establish competency ensuring system and follow up the implementation of same;

c) coordinate, through follow up and support, education and training institutions focusing on human resource development;

d) coordinate as an organized army mobilization of the Government, the public and developmental investors to ensure the prevalence of developmental good governance;

e) ensure that the recruitment and selection of the federal public servants is based on merit system;

f) establish competence and performance based pay and reward system for the public service; evaluate its effectiveness and make necessary adjustments;

g) establish a system to monitor ethics of Federal public servants', and follow up the implementation of same;

h) follow up and ensure the proper enforcement of Federal public servants' administration laws;

i) coordinate public sector capacity building activities; adopt strategies for continuous improvement of service delivery in the public sector; monitor and evaluate the implementation of same;

በ) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የውስጥ አደረጃጀት አግባብነት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

ተ) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት እንዲታጠፍ፣ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል ለማድረግ፣ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ ለማድረግ ወይም አዲስ የመንግስት መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም ለማድረግ ወይም እንደገና ለማደራጀት ጥናት በማካሄድ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ቸ) በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

ኀ) የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራር መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ያደርጋል፤ ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

ነ) በሕግ መሠረት የፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ኘ) በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በሚቀርብ ይግባኝ ላይ የፍሬ ነገር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

j) review and decide the appropriateness of the internal organizational structures of Federal Government offices; provide necessary support in conducting reform studies;

k) conduct studies and recommend to Government on the closure,merger or division of Federal Government office or for change of accountability or mandates or for the establishment of a new one or for the reorganization of the Federal Government office;

l) ensure that Federal Government offices have established and implement service delivery standards, complaint submission and handling procedures for customers;

m) ensure the development and implementation of uniform information system on human resource management of the public service and serve as a central information clearing house;

n) decide on requests for authorization of retention of public servants in service beyond retirement age;

o) give final decisions on the issue of fact on appeals of public service employees on the basis of public service laws;

ፐ) በፌደራል ደረጃ የሚከናወኑ የካይዘን አመራር የለውጥ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ በስራ ላይ ባሉ የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## ፲፰. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

፩/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኢኮኖሚ ትብብርና የፊስካል ፖሊሲዎችን በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

ለ) የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣የሂሣብ አያያዝ፣የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ በፌደራልና በክልል መንግሥታት ደረጃ የሚዘረጉ የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የፌደራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፣ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፣

p) follow up and supervise the proper execution of Kaizen based reform activities conducted at the federal level.

2/ The powers and duties given to the Civil Service Ministry by the provisions of other laws, currently in force, are hereby given to the Ministry of Public Service and Human Resource Development.

## 18. The Ministry of Finance and Economic Cooperation

1/ The Ministry of Finance and Economic Cooperation shall have the powers and duties to:

a) initiate economic cooperation policies and fiscal policies that particularly serve as a basis for taxes, and duties; and follow-up the proper implementation of same;

b) establish systems of budgeting, accounting, disbursement and internal audit for the Federal Government, and follow-up the implementation of same; ensure the harmonization of systems of budgeting, accounting, disbursement and internal audit established at the levels of both Federal and Regional Governments;

c) prepare the Federal Government budget, make disbursements in accordance with the approved budget, and evaluate the performance of the budget;

መ) የፌደራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ሠ) የውጭ ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ረ) ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በሀገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፤

ሰ) የፌደራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፤ ይጠብቃል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች (ከብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር ጋር የተያያዙትን ሳይጨምር) በዚህ አዋጅ ለገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## ፲፱. <u>የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር</u>

፩/ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

d) establish a system of procurement and property administration for the Federal Government and supervise the implementation of same;

e) mobilize, negotiate and sign foreign development assistance and loans, and follow-up the implementation of same;

f) manage and coordinate the bilateral economic cooperation with different countries as well as the relationship with International and Regional organizations set-up to create economic cooperation; follow up the impact of same on the performance of the country's economy;

g) be the depository of and safeguard the Federal Government's shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets;

2/ The powers and duties given to the Ministry of Finance and Economic Development by the provisions of other laws, currently in force, other than those related to the powers and duties of the National Planning Commission, are hereby given to the Ministry of Finance and Economic Cooperation.

## 19. <u>The Ministry of Agriculture and Natural Resources</u>

1/ The Ministry of Agriculture and Natural Resources shall have the powers and duties to:

ሀ) የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ለአርብቶ አደሩ፣ ለግል ባለሃብቱ እና በከተማ የእርሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የሥልጠና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ለ) ለገበያ የሚቀርብ የሰብል ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

ሐ) ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት ዕጽዋትና አዝርዕት ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

መ) የዕጽዋት በሽታዎች ወረርሽኝንና ተዛማጅ ተባዮችን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሠ) የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና እንዲጠበቅ፣ የጥምር እርሻ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ረ) የሰብል ምርት ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፤ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሰ) የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

ሸ) የሰብል ምርታማነትና ጥራትን የሚያረጋግጡ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ በአገር ውስጥ የሚባዙበትን ሁኔታም ያመቻቻል፤

a) promote the expansion of extension and training services provided to farmers, pastoralists, private investors and urban communities engaged in urban agriculture to improve the production and productivity of crops;

b) establish a system to ensure that any crop product supplied to the market maintains its quality standard; and follow up the implementation of same;

c) conduct quarantine on plants and seeds brought into or taken out of the country;

d) establish a system to control the outbreak of plant diseases and migratory pests;

e) promote sustainable natural resources development and protection and, expansion of agro-forestry;

f) build capacity for supplying, distributing and marketing of crop production inputs to ensure the reliability of their supply; establish and follow up the implementation of a system for quality control;

g) ensure the proper administration and control of pesticides;

h) promote the expansion of effective technologies to ensure crop productivity and quality; facilitate the domestic production capacity of the technologies;

ቀ) የሆርቲካልቸር ልማትን ያስፋፋል፤

በ) የቡና እና የሻይ ልማት እና ግብይት የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

ተ) የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ቸ) የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤና የሚጠበቅበትን እና አገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓት የሚዘረጋበትን ስልት ይነድፋል፤

ኀ) የገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ እና ለአርሶ አደሮች አገልግሎቱ ተደራሽ እንዲሆን ያመቻቻል፤

ነ) የሰብል ምርት ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

ኘ) ለግብርና ልማት አጋዥ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

አ) የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፤

ከ) የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ይመራል፤

ኸ) የግብርና ምርምር እና የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

i) expand horticulture development;

j) ensure the proper execution of functions relating to coffee and tea development and marketing activities;

k) promote the expansion of cooperative societies;

l) design mechanisms for the improvement of soil fertility, soil health protection and for establishing national soil database;

m) facilitate enabling environment for the provision of rural credit facilities and the accessibility of same to farmers;

n) establish a system whereby stake holders of crop research coordinate their activities and work in collaboration;

o) expand small-scale irrigation schemes development;

p) follow up and provide support in the establishment of a system involving rural land administration and use, and organize a national database;

q) establish and direct training centers that contribute to the enhancement of agricultural development and the improvement of rural technologies;

r) ensure the proper execution of functions relating to agricultural research and agricultural investment;

ወ) የምግብ ዋስትና እና የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚመለከቱ ተግባራትን ያስተባብራል፡፡

2/ በስራ ላይ ባሉ የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች እርሻና የተፈጥሮ ሀብትን በሚመለከት ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## ፳. የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር

1/ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍን ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ፣ ለግል ባለሃብቱ እና በከተማ እንስሳት ልማት ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የስልጠና አገልግሎቶችን ያስፋፋል፤

ለ) ለገበያ የሚቀርብ ማንኛውም እንስሳ፣ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሐ) ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት የግብአት አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፤ የጥራት ቁጥጥር ሥርአት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

መ) የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

s) coordinate activities relating to food security and job creation in the rural settings.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Agriculture by the provisions of other laws, currently in force, with respect to matters relating to crop and natural resource are hereby given to the Ministry of Agriculture and Natural Resources.

## 20. The Ministry of Livestock and Fisheries

1/ The Ministry of Livestock and Fisheries shall have the powers and duties to:

a) promote the expansion of extension and training services provided to farmers, pastoralists, private investors and urban communities engaged in livestock and fish farming to improve the productivity of the sector;

b) establish a system that ensures quality standard of any livestock or livestock product supplied to the market; and follow up implementation of same;

c) build capacity for supplying, distributing and marketing of inputs for livestock and fisheries to ensure the reliability of their supply; establish and follow up the implementation of a system for quality control;

d) establish a system that ensures access to quality veterinary services to improve the prevention and timely control of animal diseases;

ሠ) ወደ ሃገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር በሚወጡት እንስሳትና ዓሣ እንዲሁም የእንስሳትና ዓሣ ተዋጽኦ ላይ የኳራንታይን አገልግሎት ይሰጣል፤ ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ተጽዕኖዎችን ይከላከላል፤

ረ) የእንስሳትና የዓሣ እንዲሁም የእንስሳትና ዓሳ ተዋጽኦ ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሰ) የእንስሳት መድሃኒቶችና መኖ ጥራት እንዲሁም የእንስሳት ህክምና አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) የእንስሳትና የዓሣ ሀብት ልማት ምርምሮች ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሠሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

ቀ) በአርብቶ አደር አካባቢ ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ ውሃ፣ መሠረተ ልማትና የመኖ ባንኮች መስፋፋታቸውን ይከታተላል፤ የተፈጥሮ እና የመስኖ ግጦሽ መሬት ልማት እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፤

በ) የዓሣ ምርትና አቅርቦትን ያስፋፋል፤

ተ) በዓሣ ልማት ዘርፍ ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የእን ስሳትና ዓሣ ሀብትን በሚመለከት ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

e) conduct quarantine on import and export of livestock, fish and their byproducts; prevent communicable livestock diseases and the outbreak of migratory parasites;

f) establish and follow up the implementation of marketing system for livestock and fish and products of same;

g) ensure the proper administration and quality control of veterinary drugs and feeds as well as veterinary services;

h) develop a system that ensures integration and coordination of stakeholders engaged on livestock and fishery's research;

i) follow up the expansion of water resources, infrastructure and fodder banks necessary for livestock resource development in the pastoral areas; establish a system for natural and irrigated rangeland development and utilization, and organize national database

j) promote fish production and supply;

k) provide technical support for the development of modern fish production system and creation of market linkage.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Agriculture by the provisions of other laws, currently in force, with respect to matters relating to livestock and fishery are hereby given to the Ministry of Livestock and Fisheries.

**፳፩. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣ በመንግስት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፫/ በአገልግሎት፣ በግብርናና በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ስርዓት ይዘረጋል፣ይከታተላል፤

፬/ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መረጣ፣ ማላመድና ማስረጽ ተግባራትን፤ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የክህሎት ልማት እና በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያመቻቻል፤

፭/ የኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፤ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፮/ የኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ጥናት እንዲጠና ያደርጋል፤ ለተግባራዊነቱ ከትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

**21. The Ministry of Industry**

The Ministry of Industry shall have the powers and duties to:

1/ formulate policies, strategies and action plans that assist in the acceleration of industrial development, and implement same upon approval by the government;

2/ promote the expansion of industry and investment;

3/ establish system and provide support to domestic investors engaged in service, agriculture and construction sectors to transfer and engage in manufacturing sector;

4/ facilitate selection, adoption and implementation of technology, acquiring best practices, technology transfer and skills development that accelerate industrial sector development and, in general the capacity building activities for industrial development;

5/ establish systems of capacity building, research and dissemination to maintain the quality standards and competitiveness of industrial products on international market and, ensure implementation of same;

6/ cause studies to be conducted to meet the human resource demands of industrial sectors', and facilitate conditions necessary to work in partnership and cooperation with educational and research institutions to accomplish same;

፯/ ለኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ ግብዓት የሚቀርብበትን ስልት ይቀይሳል፣ የግብአት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰/ ስትራቴጂካዊ ትኩረት የሚሰጣቸውን እና ከባድ ኢንዱስትሪዎችን እውን የሚሆኑበትን መንገድ ያጠናል፣ ያመቻቻል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፱/ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ማበረታቻዎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኋላ አተገባበራቸውን ይከታተላል፤

፲/ በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠር የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ወደ መካከለኛ እና ከፍተኛ እንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፩/ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

፲፪/ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የኢንዱስትሪ ፓርኮችን፣ ዞኖችን ወይም ክላስተሮችን በሚመሠርቱበት ወቅት ተገቢውን እገዛና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫/ የኢንዱስትሪ መረጃዎች አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

7/ devise a mechanism for reliable provision of inputs for industries and, facilitate conditions necessary for linkage of provision of industrial inputs;

8/ conduct studies and facilitate the realization of industries having strategic importance and large scale industries, and follow up implementation of same;

9/ cause studies to be conduct on incentives that may assist the industrial sector to be internationally competitive, and follow up the implementation of same upon their approval;

10/ develop a working mechanism that creates linkage between small, medium and large scale industries, and provide necessary support to small and medium industries to transform them to medium and large scale industries;

11/ cause provision of assistances such as industrial extension services, technology, inputs and marketing and method of manufacturing to ensure the growth and productivity of industrial sector and, evaluate their effectiveness;

12/ provide necessary support and capacity building assistance to Regional States or City Administrations on the establishment of industrial parks, zones and clusters;

13/ establish industrial information system that promotes efficiency in industrial data collection, management and use and, follow up its implementation;

፲፬/ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ በኢንቨስትመንትና በምርት ሂደት ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፭/ የኢንዱስትሪ መስፋፋትን ለማፋጠን በሚያስ ፈልጉ የአቅም ግንባታ ተግባራት፣ በሰው ሃብት ልማትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ከተለያዩ የውጭ ሃገራት እና ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር የትብብር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

፲፮/ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ የቴክኖሎጂና የምርምር ተቋማት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ አጥንቶ ለመንግሥት ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም አፈፃፀማቸውን ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

፲፯/ የኢንዱስትሪ፣ የዘርፍና የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

፲፰/ በሌሎች ሕግጋት የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያስፈጽማል፡፡

## ፳፪. የንግድ ሚኒስቴር

የንግድ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የአገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርም ጃዎች ይወስዳል፤

፪/ የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትና የሚጠናከ ርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለላኪዎች ድጋፍ ይሰጣል፣

14/ provide support to industries in their investment activities and manufacturing processes so as to meet the environme ntal protection requirements;

15/ put in place system of cooperation with foreign countries and development assistance providing organizations in capacity building, human resource development and technology transfer that help to accelerate industrial development and, follow up the implementation of same;

16/ conduct studies and submit for Government decision on the establishhment of technol ogical and research institutions that help acceleration of industrial development and, upon approval supervise and follow up their implementations of same;

17/ encourage the establishment of sectoral and professional associations, and strengthen those already established;

18/ execute powers and duties given to it by the provisions of other laws.

## 22. The Ministry of Trade

The Ministry of Trade shall have the powers and duties to:

1/ promote the expansion of domestic trade and take appropriate measures to maintain lawful trade practices;

2/ create conducive conditions for the promotion and development of the country's export trade and extend support to exporters;

፫/ የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፣ ዋጋ አሳንሰው የሚልኩ እንዲሁም አሳንሰው ወይም አስበልጠው በሚያስመጡ ላይ በሕግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤

፬/ የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፣ ድርድሮችን ያስተባብራል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ያስፈጽማል፤

፭/ ፀረ ውድድር ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ በሕግ አግባብ ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፤

፮/ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ለተሰጠባቸው ዓላማዎች መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፯/ የአክሲዮን ማኅበራት የባለአክሲዮኖችንና የኅብረተሰቡን ጥቅም በሚያስከብር ደረጃ እንዲቋቋሙና እንዲሠሩ ድጋፍ ይሰጣል፣ ክትትል ያደርጋል፤

፰/ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

3/ establish a system that enable to ascertain that export or import goods are sold or bought at the appropriate price; make follow ups in collaboration with the concerned executive bodies, and take measures in accordance with the law against those who export by under invoicing as well as import under or over invoicing;

4/ establish foreign trade relations, coordinate trade negotiations, sign trade agreements in accordance with Law and implement same;

5/ establish and follow up the implementation of comprehensive system for the prevention of anti-competitive trade practices provide protection to consumers in accordance with the law;

6/ provide commercial registration and business licensing services in accordance with the relevant Laws and control the use of business licenses for unauthorized purposes;

7/ provide support for, and monitor, the establishment and operation of share companies with a view to protect the interests of share holders and the society;

8/ undertake and submit to the Council of Ministers price studies relating to basic commodities and services that have to be under price control and, upon approval, follow up the implementation of same;

፱/ የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መተግበሩን ይቆጣጠራል፣ አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

፲/ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ያግዳል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

፲፩/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙበት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፪/ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ በአፈጻጸም ላይ የሚወያይ ጉባኤ ይጠራል፣ መድረኩንም ይመራል፤

፲፫/ የአገሪቱን የንግድ መረጃዎች ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፲፬/ የሸማቾችን ጨምሮ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶችን እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፡፡

፳፫. **የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር**

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የሀገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲፀድቁም ተግባራዊ እንዲደረጉ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ይገመግማል፤

9/ establish the legal metrological system of the country, regulate its enforcement and coordinate the concerned regulatory bodies;

10/ control the qualities of export and import goods; prohibit the importation and exportation of goods that do not conform with the required standards, and work in collaboration with the concerned organs;

11/ control the compliance of goods and services with the requirements of mandatory Ethiopian standards, and take measure against those found to be below the standards set for them;

12/ cause the coordinated enforcement of standards applied by other enforcement bodies, organize and direct implementation review conferences;

13/ organize the trade data of the country, and disseminate same to the concerned bodies;

14/ encourage the establishment of chambers of commerce and sectoral associations, including, consumers' associations, and strengthen those already established.

23. **The Ministry of Science and Technology**

The Ministry of Science and Technology shall have the powers and duties to:

1/ prepare national science and technology research and development programs based on the country's development priorities, and upon approval by the Government, provide necessary support for their implementation; follow up and evaluate same;

፪/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክ ኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ቴክኖሎጂዎችን ለማፈ ላለግ፣ለመምረጥ፣ለማስገባት፣ለመቀመር፣ለመጠቀም እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፫/ በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ ሞዲፋይ የማድረግና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣዩ ሥራ እንቅስቃሴም እንዲውሉ ያደርጋል፤

፬/ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤ የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋጋጣል፣

፭/ የሣይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን አመለካቾችንም ያዘጋጃል፣ ለአገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፤

፮/ በመንግሥትና በግል የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፯/ የሀገሪቱን የረዥም ጊዜ የሣይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኢኖቬሽንና የጥራት መሠረተ ልማት የሰው ኃይል ልማት ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

2/ in cooperation with the concerned bodies, establish a system for technology need assessment, identification, acquisition, packaging, utilization and disposal, and follow up the implementation of same;

3/ register technology transfers made in every sector, coordinate codification and technology capability accumulation efforts, and ensure successive use of same;

4/ coordinate science and technology development activities and national research programs; ensure that research activities are conducted in line with the country's development needs;

5/ organize science, technology and innovation data base, compile information, set national standards for information management, prepare and ensure the application of science and technology innovation indicators;

6/ facilitate interaction and collaboration among Government and Private Higher Education and Research institutions and industries with a view to enhancing research and technological development;

7/ prepare and follow up the implementation of the country's long-term human resource development plans in the fields of science, technology, innovation and quality infrastructure; cooperate with the concerned organs to ensure that the countries educational curricula focus on the development of science and technology;

፰/ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ በሣይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም የሚገነባበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ድጋፍ ይሰጣል፤

፱/ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች እድገት አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲/ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችንም ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

፲፩/ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋ ጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ያበረታታል፤ ይደግፋል፤

፲፪/ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቴክኖሎጂ ፍላጐትን ይለያል፤ አግባብነት ያላቸውና ዕሴት የሚጨምሩ የቴክኖሎጂ መረጃ ዎችን አደራጅቶና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል፤

፲፫/ የብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማትና የጨረራ መከላከያ አገልግሎቶች፣ የደረጃዎች ምደባ፣ የተስማሚነት ምዘና፣ የአክርዲቴሽን ሥራዎች እና የሥነ-ልክ አገልግሎቶች እንዲሁም የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባና አስተዳደር ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

፲፬/ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ነክ ተቋማትን ይመራል፤ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸውን አስተዋጽዖ ያረጋግጣል፡፡

8/ facilitate capacity building of public and private sector institutions and professionals involved in science and technological activities;

9/ establish and implement a system for granting prizes and incentives to individuals and institutions who have contributed to the advancement of science, technology and innovations;

10/ establish, coordinate and support councils that facilitate the coordination of research activities;

11/ encourage and support professional associations and academies that may provide pivotal contribution to the development of science and technology;

12/ in collaboration with stakeholders, identify the technology demand to ensure the transfer and development of technology; disseminate organized and well elaborated appropriate and value added technology information to users;

13/ ensure the proper implementation of activities relating to National quality infrastructure and radiation protection services, standardization, conformity assessment, accreditation activities and metrology services, as well as the registr ation and administration of intellectual property;

14/ lead science and technology related institutions and ensure their contribution to the economic development of the country.

## ፳፬. የትራንስፖርት ሚኒስቴር

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች መዘርጋታ ቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን ያረጋግጣል፤

፪/ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን ስታንዳርድ ያወጣል፤ የአጠቃቀም፣ የአያያዝና የአስተዳደር ሥርዓቶችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤

፫/ የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎ ቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን እንዲሁም የሀገሪቱን የልማት ስትራቴጂዎች በተሟላ ሁኔታ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፬/ የአየር፣ የባህርና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎ ቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፭/ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶችና አገልግ ሎቶች በአካባቢ አየር ፀባይ ለውጥ ላይ የሚኖራ ቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፮/ የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የተመለከቱ የትራንዚት ሥራዎችን ይቆጣጠራል፤ የሀገሪቷን የሎጂስቲክስ ሥርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፯/ የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤

፰/ የሀገሪቷን የትራንስፖርት መረጃዎች ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

## 24. The Ministry of Transport

The Ministry of Transport shall have the powers and duties to:

1/ ensure that transport infrastructures are constructed, upgraded and maintained;

2/ set standards for transport infrastr uctures; determine the usage, mainten ance, and administration system of transport infrastructures and ensure their implementation;

3/ ensure the integration, promotion and accessibility of land, air, and water transport services and that they serve the country's development strategy in a comprehensive manner;

4/ ensure the establishment and impleme ntation of regulatory frameworks to guarantee the provision of reliable and safe land, air, and water transport services;

5/ identify and implement measures that enables to mitigate the impact of transport infrastructures and services on climate change;

6/ regulate transit services related to import and export of goods; ensure the logistic services of the country is prompt and competitive;

7/ ensure that the investigation of aircraft accidents are carried out in accordance to the acceptable standards;

8/ organize the transport data of the country, disseminate same to concerned bodies;

፱/ የመሬት ውስጥ ለውስጥ ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን ስታንዳርድ ያወጣል፤ ተግባራዊነታቸውን ይቆጣጠራል፤

፲/ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎ ቶችን የተመለከቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

፲፩/የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ይከታተላል፡፡

## ፳፭. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የመገናኛ አገልግሎቶችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፪/ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲን በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፫/ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግ ሎቶች ጥራታቸው፣ደህንነታቸውና አስተማማ ኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

፬/ ለቴሌኮሙኒኬሽን አልግሎቶች የሚጠየቀውን ክፍያ ይቆጣጠራል

9/ formulate standards for tube line transport infrastructure and services, and ensure implementation of same;

10/ ensure utilization, expansion, and reinforcement of advanced technologies and practices in the countries transport infrastructures and services;

11/ follow up the activities of the Ethio-Djibouti Railways in accordance with the agreements concluded between the two countries.

## 25. The Ministry of Communications and Information Technology

The Ministry of Communications and Information Technology shall have the powers and duties to:

1/ promote the expansion of communication services and the development of information technology;

2/ facilitate the creation of institutional capacity for the effective implementation of information technology development policy;

3/ set and implement standards to ensure the provision of quality, reliable and safe communication and in formation techno logy services;

4/ regulate the rate of telecommunication service charges;

፭/ የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎቶች በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፮/ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ያረጋጋጣል፤

፯/ በመንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ከመገንባትና ከማቀናጀት አንፃር የመንግሥት የዶሜይን ስም ይደለድላል፣ አድራሻ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፤

፰/ የአገሪቱን የከፍተኛውን ደረጃ መለያ ዶሜይን ስም ሀገራዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመለከታ ቸውን ያስተባብራል፣ ለአፈፃፀሙም እገዛ ያደርጋል፤

፱/ መረጃ በተፋጠነ መልክና በተመጣጠነ ወጪ ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲/ በፌደራልና በክልል መንግሥታት ተቋማት መካከል እንዲሁም በፌደራልም ሆነ በክልል ተቋማት ውስጥ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፩/ ለሕዝብ አልግሎት በመስጠት ላይ ያተኩሩ መሠረታዊ ሲስተሞችና አልግሎቶች በኮምፒዩተር የተደገፉ እንዲሆኑና ደረጃ በደረጃም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪/ በሥራ ላይ የሚውሉ የኮምፒዩተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች ከቴክኒክና አሠራር አኳያ መቀናጀትና መናበብ መቻላቸውን ያረጋግጣል፤

5/ Provide license and regulate telecom munication and postal service operators;

6/ ensure the technical compatibility of telecommunication equipments;

7/ assign and monitor Government domain names and register addresses to develop and coordinate Government institutions' information system;

8/ coordinate all stakeholders for the creation and proper utilization of country code top level domain, and facilitate the proper implementation of same;

9/ facilitate the creation of fast and affordable information access;

10/ follow up, and provide necessary support for, the implementation of modern information network between and within Federal and Regional Government institutions;

11/ ensure mission critical systems and services in public sector are computerized and online services are gradually available to users;

12/ ensure the integration and interoperability of operational and forthcoming computer networks and applications;

፲፫/ በመንግሥታዊ ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፤

፲፬/ በሌሎች የመንግሥት አካላት ብቃታቸው ለማይረጋገጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎችና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፲፭/ የቴሌኮሙኒኬሽን፣የፖስታ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፲፮/ በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶች እንዲ ስፋፉ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤

፲፯/ በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚሰጥ ትምህርት እንዲስፋፋ ከትምህርት ተቋሞች ጋር ይተባበራል፤

፲፰/ በመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የመገና ኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማትን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል የሥልጠና እና የፕሮጀክት አስተዳደርና አፈጻጸም ምክር ይሰጣል፣ መመሪያ ያወጣል ስለአፈጻጸሙም ክትትል ያደርጋል፤

፲፱/ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ ምቹ ሁኔታዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፳/ ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀም ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፤

13/ support the coordinated and secured information flow and exchange between Government institutions, follow up their proper applications;

14/ issue certificates of competence to information technology professionals and entities whose accreditations do not fall under the jurisdiction of other government organs;

15/ issue directives necessary for regulating telecommunication, postal and information technology services;

16/ conduct research and studies for the advancement of new technologies and services in the communication and information technology field;

17/ collaborate with educational institutions to promote education in the fields of communication and information technology;

18/ give training and, advice on project administration and implementation to facilitate the utilization of communication and information technology in Government organization; issue directives and follow up implementation of same;

19/ design favorable conditions for the development of communication and information technology industry and cause implementation of same;

20/ authorize and supervise the use of radio frequencies allotted to Ethiopia;

፳፩/ ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያወጣል፣ ቁጥሮችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀማቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፪/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎችን ያስከፍላል፡፡

**፳፮. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር**

፩/ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) አገራዊ ስፓሻል ፕላን በመስራት የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ለክልሎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፤ የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤

ሐ) ከተሞች የልማት ማዕከል ሆነው በአካባቢያቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

መ) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም ልማታዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተሞች ልማት መስክ የማሠልጠኛና የምርምር ማዕከሎችን ያደራጃል፤

21/ establish national telecommunication numbering plan, allocate and administer numbers and supervise efficient use thereof;

22/ collect service fees in accordance with rates approved by the Council of Ministers.

**26. The Ministry of Urban Development and Housing**

1/ The Ministry of Urban Development and Housing shall have the powers and duties to:

a) establish integrated national urban system by preparing national spatial plan and follow up implementation of same; provide capacity building support to Regional Governments;

b) undertake studies relating to urbanization, and set criteria for categorization and role definition of urban centers;

c) provide all-round and coordinated support to urban centers to make them development centers capable of influencing their surroundings;

d) provide capacity building support to urban centers for improving their service delivery and ensuring developmental good governance; and where necessary, organize training and research centers in the field of urban development;

ሠ) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ በሚመለከታቸው አካላት እንዲጸድቁ ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያግዛል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

ረ) ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፤

ሰ) ዜጎች ከአቅማቸው ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሚመለከ ታቸው አካላት እንዲጸድቁ ያደርጋል፣ ለተግባራዊነ ታቸውም ለክልሎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ሸ) የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፤

ቀ) የከተማ የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

በ) ከተሞች በፕላን እንዲመሩ እገዛ እና ክትትል ያደርጋል፤

ተ) አዳዲስ የከተማ ክፍሎች በነባር ከተሞች ውስጥ እና በዙሪያቸው የሚፈጠሩበትን ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይደግፋል፤

ቸ) በአገር አቀፍና በክልል የከተማ መሬትን በማሰባሰብና በማልማት በቀጣይነት፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት መርህ ለማቅረብ የሚችሉ ተቋማት እንዲደራጁ ያጠናል፤

e) in collaboration with Regional States, undertake studies for the integration of urban and rural development activities; cause their approval by the concerned organs; assist and follow-up the implementation of same;

f) follow up the activities of city administrations accountable to the Federal Government;

g) undertake studies for setting general directions for citizens to acquire residential houses compatible with their own income; cause their approval by the concerned organs; provide capacity building support to regions for the implementation of same;

h) undertake studies for the integration of urban development with poverty reduction activities, and support the implementation of same;

i) ensure food security and job creation in the urban settings;

j) provide support for plan-led urbanization and follow-up its implementation;

k) devise strategy that support the development of new township in the cities and the surroundings; cause its approval by the concerning organ, support implementation of same;

l) undertake study to establish institutions at the Federal and Regional levels that will be responsible to acquire, develop and supply urban land in a continuous,

በሚመለከታቸው አካላት እንዲጸድቁ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ኀ) በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤

ነ) የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤

ኘ) በከተሞች የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

አ) የከተማ ሞቢሊቲ ከመሬት አጠቃቀም ጋር ተሳስሮ በስልጠት እንዲመራ ጥናት ያደርጋል፣ ይደግፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ከ) የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፣ የትግበራ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ኸ) የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ወ) በተልዕኮ ለሌሎች ዘርፎች የተሰጡና በከተማ ምህዳር የሚተገበሩ እና ለከተሞች ልማት ፍጥነትና ውጤታማነት ፋይዳ ያላቸው ተግባራትን ይዘትና ሂደት የከተማ ቅኝት ለማስያዝ የማስተባበር ሥራ ያከናውናል፤

transparent and accountable manner; cause their approval by the concerned organs; follow up implementation of same;

m) provide support to ensure the supply of developed urban land in accordance with the demand;

n) build a cadastre and immovable property market systems that ensures transparency and accountability to enhance a free market economy;

o) ensure integrated infrastructure provision and service delivery in the urban setting;

p) undertake studies that ensure integrated and efficient urban mobility and support and follow up its implementation;

q) set standards for urban cleansing, beautification and greenery development, support and follow up its implementation;

r) undertake study to establish urban development finance improvement system; cause its approval by the concerned organ; sourcing urban development funding; provide implementation support and institutional capacity building;

s) coordinate the content and course of activities of other sectors that will be implemented within the urban sites and that may have big implications for the accelerated efficient development urban settings so as to orient with the urban setting;

ዘ) ለሌላ የመንግሥት አካል በሕግ የተሰጠ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የከተማ ልማትና ቤቶችን በሚመለከት ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## ፳፯. የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

፩/ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፤

ለ) በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤

ሐ) በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

መ) በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፤ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

t) without prejudice to the powers given by law to any other Government organ, ensure the proper administration of houses owned by the Federal Government.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Urban Development, Housing and Construction by the provisions of other laws, currently in force, with respect to matters relating to urban development and housing, are hereby given to the Ministry of Urban Development and Housing.

## 27. The Ministry of Construction

1/ The Ministry of construction shall have the powers and duties to:

a) without prejudice to the powers given by law to other organs, set and follow up the compliance of standards for construction works;

b) create conducive conditions for the development of internationally competitive construction industry;

c) provide necessary support in the preparation of designs and contract documents and also supervision for building constructions financed by the Federal Government;

d) register and issue certificates of professional competence to engineers and architects engaged in the construction sector; determine the grades of contractors and consultants, and issue certificates of competence to those operating in more than one Regional States;

ሠ) አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ረ) በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤

ሰ) የህንጻ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ኮንስትራክሽንን በሚመለከት ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

**፳፰. የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር**

፩/ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የውሃ ሀብትና የኤሌክትሪክ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ለ) የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

e) design national construction enterprises strengthening strategy to ensure competence and viability; follow up the implementation of same;

f) undertake research for improving the types and qualities of local construction materials;

g) ensure the availability of appropriate organizational set-up, systems and human resource required for the implementation of building codes and standards in the cities; and follow up and support the implementation of same.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Urban Development, Housing and Construction by the provisions of other laws, currently in force, with respect to matters relating to construction are hereby given to the Ministry of Construction.

**28. The Ministry of Water, Irrigation and Electricity**

1/The Ministry of Water, Irrigation and Electricity shall have the powers and duties to:

a) promote the development of water resources and electricity;

b) undertake basin studies and verify the country's ground and surface water resource potential in terms of volume and quality, and facilitate the utilization of same;

ሐ) ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፣

መ) በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ሠ) የመካከለኛና የከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ረ) ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት እንዲተላለፉ ካልተደረገ በስተቀር፣ በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል

ሰ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤

ሸ) የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

ቀ) የሀገሪቱ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

በ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) በተጠቀሱት የውሃ አካሎች ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል፤

c) determine conditions and methods required for the optimum and equitable allocation and utilization of water bodies that flow across or lie between more than one Regional States among various uses and the Regional States;

d) undertake studies and negotiations of treaties pertaining to the utilization of boundary and trans-boundary water bodies, and follow up the implementation of same;

e) cause the carrying out of study, design and construction works to promote the expansion of medium and large irrigation dams;

f) administer dams and water structures constructed by Federal budget unless they are entrusted to the authority of other relevant bodies;

g) in cooperation with the appropriate organs, prescribe quality standards for waters to be used for various purposes;

h) support the expansion of potable water supply coverage; follow up and coordinate the implementation of projects financed by foreign assistance and loans;

i) promote the growth and expansion of the country's supply of electric energy;

j) issue permits and regulate the construction and operation of water works relating to water bodies referred to in paragraphs (c) and (d) of this sub-article;

ተ) የሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የውሃ ሀብትንና ኤሌክትሪክን በሚመለከት ለውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

**፳፱. <u>የማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር</u>**

፩/ የማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

ለ) የማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣እንዲጠ በቁና ለተጠቃ ሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፣

ሐ) ለማዕድን፣ለነዳጅና ለተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኢንቨስትመንት ያበረታታል፣

መ) ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ ያደርጋል፣

ሠ) የማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችን እንዳስፈላጊነቱ ያደራጃል፣

k) ensure the proper execution of functions relating to meteorological services.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Water, Irrigation and Energy by the provisions of other laws, currently in force, with respect to water resource and electricity, are hereby given to the Ministry of Water, Irrigation and Electricity.

**29. <u>The Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas</u>**

1/ The Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas shall have the powers and duties to:

a) promote the development of mining, petroleum and natural gas;

b) ensure the proper collection, maintenance and accessibility to users of data on minerals, petroleum and natural gas;

c) encourage investment through creating conducive conditions for exploration and mining operations;

d) regulate, in cooperation with the concerned organs, the market for precious and ornamental minerals produced at traditional level and small-scale mining operations comply with law;

e) organize, as may be necessary, research and training centers that may assist the enhancement of the development of mining, petroleum and natural gas;

ረ) በማዕድን፣በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሠማሩ የግል ባለሃብቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ በገቡት ውል መሠረትም ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

ሰ) የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ምርቶችን የጥራት ደረጃ ያረጋግጣል፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ተቋሞችን ደረጃ ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

ሸ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የነዳጅና መጠባበቂያ ክምችትን መጠን ይወስናል፣ ክምችቱ እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፤

ቀ) በባህላዊ መንገድ ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያደራጃል፣ አቅማቸውን ይገነባል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ማዕድንን፣ ነዳጅንና የተፈጥሮ ጋዝን በሚመለከት ለማዕድን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

**፴. <u>የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር</u>**

፩/ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤

f) issue licenses to private investors engaged in exploration and mining operations, and ensure that they conduct mining and exploration operations and meet financial obligations in accordance with their concession agreements;

g) ensure the quality standards of petroleum and natural gas products, set standards for petroleum storage and distribution facilities, and follow up the enforcement of same;

h) in cooperation with the appropriate organs, determine the volume of petroleum reserve and ensure that it is maintained;

i) in cooperation with the concerned organs organize and build the capacity of individuals engaged in traditional mining operation.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Mines by the provisions of other laws, currently in force, with respect to mines, petroleum and natural gas, are hereby given to the Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas.

**30. <u>The Ministry of Environment, Forest and Climate Change</u>**

1/ The Ministry of Environment, Forest and Climate Change shall have the powers and duties to:

a) coordinate activities to ensure that the environmental objectives provided under the Constitution and the basic principles set out in the Environmental Policy of the Country are realized;

ለ) በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎች መርሐ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሥርዓቱ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

ሐ) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ፍትህን በሚያራምድና ከሚገኘው ጥቅም ትልቁን ድርሻ በእርምጃው ለሚነኩ ማህበረሰቦች በሚያስገኝ የስርየት እርምጃ ከደን ምንጣሮና ጉስቁልና ሊከተል ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የመቀነሻ ሥርዓት ያዘጋጃል፤

መ) ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በየዘርፉና በየክልሉ ለመገንቢያ የሚውል ሃብት የሚያስገኙ ተግባራት ዝግጅትን ያስተባብራል፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍንና የምክር አገልግሎትን ይሰጣል፤

ሠ) በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት ለልማት ፕሮጀክት እና ፕሮግራም የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ እና ፕሮግራሙ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከተው የዘርፍ የፈቃድ ሰጪ አካል ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሣኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ረ) ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሃብቶች መሠረት፣ ከበረሃማነት፣ ከደን፣ ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ ከኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እና ከሰው ሰራሽ የአካባቢ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ጋር በተያያዘ ያፀደቀቻቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን በየዘርፉና በየአስተዳደር

b) establish a system and follow up implementation for undertaking environmental impact assessment or strategic environmental assessment on social and economic development polices, strategies, laws, programmes and project set by the government or Privet;

c) prepare a mechanism that promotes social, economic and environmental justice and channel the major part of benefit derived thereof to the affected communities to reduce emissions of greenhouse gases that would otherwise have resulted from deforestation and forest degradation;

d) coordinate actions on soliciting the resources required for building a climate resilient green economy in all sectors and at all Regional levels; as well as provide capacity building support and advisory services;

e) establish a system for evaluating and decision making, in accordance with the Environmental Impact Assessment Proclamation, the impacts of implementation of investment programs and projects on environment prior to approvals of their implementation by the concerned sectoral licensing organ or the concerned regional organ;

f) prepare programmes and directives for the synergistic implementation and follow up of environmental agreements ratified by Ethiopia pertaining to the natural resources base, desertification, forests,

እርከኑ በመተግበር ወቅት የድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነትንና ክፍተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ መርሐግብሮችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ መተግበራቸውንም ይከታተላል፤

ሰ) በዓለም አቀፍ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ በዘርፉ አገራዊ ምላሽን በማስተባበሩ በኩል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣ እንደአግባቡ ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን፣ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፤ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ) አደገኛ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

hazardous chemicals, industrial wastes and anthropogenic environmental hazards with the objective of avoiding overlaps, wastage of resources and gaps during their implementation in all sectors and at all governance levels;

g) take part in the negotiations of international environmental and climate change agreements and, as appropriate, initiate a process of their ratification; play key role in coordinating the nationwide responses to the agreements;

h) formulate or initiate and coordinate the formulation of policies, strategies, laws, guidelines and programs to implement international environmental agreements to which Ethiopia is a party; and upon appr oval, ensure their implementation;

i) formulate environmental safety policies and laws on the production, importation, management and utilization of hazardous substances or wastes, as well as on the development of genetically modified organisms and the importation, handling and utilization of genetically modified organisms or alien species, and ensure their implementation;

በ) በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓቶችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ እንደሁኔታውም በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤

ተ) ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፤

ቸ) የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

ኀ) የአካባቢና የደን አያያዝን፣ በጥቅም ማዋልንና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን የሚያራምድ እንዲሁም አረንጓዴ የሥራ ዕድልን የሚፈጥር ምርምርንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያስተባብራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ራሱ ያካሂዳል፤

ነ) አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢና የደን ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌዴራሉ ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

j) prepare or cause the preparation of environmental cost benefit analysis and formulate an accounting system to be integrated in development plans and investment programs, as the case may be, monitor their application;

k) propose incentives or disincentives to discourage practices that may hamper the sustainable use of natural resources or the prevention of environmental degradation or pollution;

l) establish an environmental infor mation system that promotes efficiency in environmental data collection, management and use;

m) coordinate, and as may be appropriate, carry out research and technology transfer activities that promotes the sustainability of the environment and the conservation and use of forest as well as the equitable sharing of benefits accruing from them while creating opportunities for green jobs;

n) in accordance with the provisions of the relevant laws, enter any land, premises or any other place that falls under the Federal jurisdiction, inspect anything and take samples as deemed necessary with a view to discharging its duty and ascertaining compliance with the requirements of environmental protection and conservation of forest;

ኘ) የሀገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፤

አ) መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፤ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፤

ከ) አነስተኛና ሰፋፊ የደን ልማት፣ ቀርከሀን ጨምሮ በግል፣ በወል ይዞታ እና በተፋሰስ ውስጥ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ኸ) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን እንዲጠበቅና እንደአስፈላጊነቱ ዘላቂ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ወ) የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶች እንዲያገግሙና የአካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዲሻሻል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች አካባቢንና ደንን በሚመለከት ለአካባቢና ደን ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

o) prepare and disseminate a periodic report on the state of the country's environment and forest as well as climate resilient green economy;

p) promote and provide non-formal environmental education programs, and cooperate with the competent organs with a view to integrating environmental concerns in the regular educational curricula;

q) establish a system for development and utilization of small and large scale forest including bamboo on private, communal and watershed areas, and ensure implementation of same;

r) establish a system for protection and, as the case may be, for sustainable utilization of the natural forest resources of the country; and ensure its implementation;

s) establish a system to rehabilitate degraded forest lands and ensure its implementation to enhance their environmental and economic benefits.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Environment and Forest by the provisions of other laws, currently in force, with respect to matters relating to the environment and forest, are hereby given to the Ministry of Environment, Forest and Climate Change.

**፴፩. <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር</u>**

፩/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) ተጠሪነታቸው ለሌላ ተቆጣጣሪ አካል የሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የኮርፖሬት አስተዳደር እና የፋይናንስ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ለ) ተጠሪነታቸው ለሚኒስቴሩ እንዲሆን የተወሰነ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፡-

(፩) መንግሥት ከነደፋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም የኢኮኖሚ ግቦች አንፃር የተቃኘ ስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፣ ያፀድቃል፣አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣

(፪) በኢኮኖሚ ውስጥ ተገቢ ድርሻቸውን ለመወጣት ሊመሩ የሚችሉበትን ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር አሠራር ይዘረጋል፣ ለግብ ስኬታቸውም መሠረታዊ አቅጣጫ ዎችን ይነድፋል፣ ሥራ ላይ እንዲውልም ያደርጋል፣

(፫) የትርፍ ድርሻ ክፍያ ፖሊሲ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ይነድፋል፣ ሥራ ላይ እንዲውልም ያደርጋል፣

(፬) በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያላቸውን ተወዳዳሪነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሻሽሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የመረጃ ድጋፍ ይሰጣል፣ በገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ በመመሥረት የልማት ድርጅቶች ቦንድ የሚያወጡበትንና የሚገዙበትን እንዲሁም ከውጭና ከሀገር ውስጥ ብድር የሚወስዱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

**31. <u>The Ministry of Public Enterprises</u>**

1/ The Ministry of Public Enterprises shall have the Powers and duties to:

a) oversee and assist the corporate management and financial performance of the public enterprises accountable to another supervising authorities;

b) with respect to public enterprises accountable to it:

(1) ensure that they have developed strategic and annual plan consistent with policies, strategies and economic goals of the government, approve such plans and monitor implementation of same;

(2) establish a system to enable them play appropriate role in the economy, develop modern corporate management, design proper guidelines that help them achieve their goals, and ensure the implementation of same;

(3) develop dividend policy with other relevant government bodies and implement such policies;

(4) create conducive conditions, and provide them with the necessary information to enhance their competitiveness domestically and abroad; assist them in the issuance of bonds as well as in borrowing from domestic and foreign sources pursuant to the guidelines and policy directives of the Ministry of Finance and Economic Cooperation;

(፭) ግልፅ የአሠራር ሥርዓት እንዲከተሉ ያግዛል፤ ወቅታቸውን የጠበቁ ትክክለኛ የፋይናንስና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች የሚያቀርቡበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

(፮) የፋይናንስ አጠቃቀም እና የብድር ሁኔታዎችን በቅርብ ይከታተላል፣ ስለፋይናንስ አፈጻጸማቸውም ተገቢውን ሪፖርት በማዘጋጀት፣ ለሚመለከታቸው ያሠራጫል፤

(፯) ካፒታል ለማሳደግ የሚያቀርቡትን ጥያቄ ይመረምራል፤ ለመንግሥት የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ያስወስናል፤ አፈጻጸሙንም በቅርብ ይከታተላል፤

(፰) የቦርድ አባላትን ይመድባል፣ ያነሳል፣ ሊከፈላቸው የሚገባውንም አበል ይወስናል፤ የቦርድ አሰያየምና አነሳስ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ የልማት ድርጅቶች ሙያው ክህሎቱና መልካም ስብዕና ባላቸው ኃላፊዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

(፱) እንዲፈርሱ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ወይም እንዲሸጡ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ይህንን የተመለከተ ግልፅ መመሪያም ያዘጋጃል፤

(፲) ለትርፍ ብቻ የማይሰሩ ሲሆንና እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንዲችል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

(5) assist them to follow transparent procedures; develop a system under which they issue timely and proper financial and performance reports;

(6) closely monitor utilization of finance and performance of loans and distribute to relevant government agencies reports on their financial performance;

(7) evaluate their requests for increase of capital; submit its recommendations to the Government for approval, and closely follow up implementation of same;

(8) appoint and remove members of board of directors and determine their allowances; issue a directive on appointment and removal of members of board of directors; develop a system which enable public enterprises be managed by persons who have the proper qualification, skill and ethical behavior;

(9) submit proposals to the Government on their dissolution, amalgamation, or division or sale; and issue a directive to make the process transparent;

(10) help those, the objectives of which go beyond profit making, to obtain financial support from the Government where necessary;

(፲፩) ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የተገኘው የምርምር ውጤት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

(፲፪) የሚማማሩበትን መድረክ አዘጋጅቶ ልምድ እንዲለዋወጡ ያደርጋል፤ ራሱም የድርጅቶቹን አቅም የሚያሳድጉ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

ሐ) ለኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን እያጠና በመንግሥት ልማት ድርጅትነት እንዲቋቋሙ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤ መስፋፋት የሚኖርባቸውን ነባር የልማት ድርጅቶች በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

መ) በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ መንግሥት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮ ችን ያከናውናል::

፪/ ለሚኒስቴሩ ተጠሪ የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም ወደ ግል ይዞታ የሚዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና የአክሲዮን ድርሻዎችን በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፪/፲፱፻፺፮ ለፕራይቬታይዜሽን ቦርድ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## ፴፪. <u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

(11) facilitate conditions under which they allocate sufficient budget for research and innovation and disseminate findings of the research;

(12) create a forum under which they exchange their experiences, and carry out training programs that help build their capacity;

c) carry out studies to identify projects that can contribute to economic and social development and propose to the Government the establishment of new public enterprises, and when approved implement same; based on studies conduct expansion of existing public enterprises;

d) carry out other duties to protect the interest of the Government in public enterprises.

2/ With respect to public enterprises made accountable to it, the powers and duties given to a Supervising Authority of Public Enterprises by Proclamation No. 25/1992, and with respect to public enterprises and shares to be privatized, the powers and duties given to the Privatization Board by Proclamation No. 412/2004 are hereby given to the Ministry of Public Enterprises.

## 32. <u>The Ministry of Education</u>

The Ministry of Education shall have the powers and duties to:

፩/ የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፣

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣

ለ) አጠቃላይ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣

ሐ) የመምህራንን አነስተኛውን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፣

መ) የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን አነስተኛውን ደረጃ ያወጣል፣

፫/ የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፣

፬/ በየደረጃው ባሉ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ያረጋግጣል፣

፭/ የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣ የውጤት ሪከርዶች ይይዛል፣ የውጤት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

፮/ የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂን ይቀርጻል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

፯/ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፰/ ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ሀገራዊ የአህዝቦት ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

1/ set education and training standards, and ensure the implementation of same;

2/ without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article:

a) formulate a national qualification framework;

b) formulate a general framework of curricula for education;

c) set minimum educational qualification requirements for school teachers;

d) set minimum standards for education and training institutions;

3/ expand and lead higher education;

4/ ensure that quality and relevant education and training have been offered at all level of the educational and training system;

5/ prepare and administer national examinations based on the country's education and training policy and curricula; maintain records and issue certificates of results;

6/ develop national technical and vocational education and training strategies and ensure their implementation;

7/ ensure that student admissions and placements in public higher education institutions are equitable;

8/ publicize national performance in education and training.

**፴፫. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የጤናውን ዘርፍ ልማት ሀገራዊ ፕሮግራም ይነድፋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፪/ የጤና አልግሎት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ ከውጭ በሚገኝ እርዳታ ብድር የሚከናወኑ የጤና ፕሮግራሞችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፫/ አገራዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፬/ ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ነታቸውን ይከታተላል፤

፭/ ሀገራዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፮/ የሕብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የመከላከል እርምጃ ይወ ስዳል፣ የሌሎችንም እርምጃዎች ያስተባብራል፣

፯/ በሃገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የሕክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፰/ የጤና ሥርዓቱን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ድጋፍ ያደርጋል፤

፱/ የፌደራል ሆስፒታሎችን አስተዳደር በበላይነት ይቆጣጠራል፤ የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ሆስ ፒታሎችን አቅም በማጎልበት ረገድ ተባብሮ ይሠራል፤

**33. The Ministry of Health**

The Ministry of Health shall have the powers and duties to:

1/ formulate the country's health sector development program; follow up and evaluate the implementation of same;

2/ support the expansion of health services coverage; follow up and coordinate the implementation of health programs financed by foreign assistance and loans;

3/ direct, coordinate and follow up implementation of the country's health information system;

4/ devise and follow up the implementation of strategies for the prevention of epidemic and communicable diseases;

5/ follow up and coordinate the implement tation of national nutrition strategies;

6/ take preventive measures in the events of emergency situations that threaten public health, and coordinate measures to be taken by other bodies;

7/ ensure adequate supply and proper utilization of essential drugs and medical equipment in the country;

8/ prepare the country's health services coverage map; provide support for the expansion of health infrastructure;

9/ supervise the administration of federal hospitals; collaborate on the capacity building activities of the federal university hospitals;

፲/ በሀገሪቱ ውስጥ የሚሰጠው የጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

፲፩/ የሀገሪቱን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪/ አግባብነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፲፫/ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደር ደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

፲፬/ ሀገራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱን ይመራል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፡፡

፴፬. **የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር**

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲጠበቅ፣

ሀ) የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

ለ) የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

ሐ) አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

መ) በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲለመዱ ያደርጋል፤

10/ collaborate with the appropriate bodies in providing quality and relevant health professional trainings within the country;

11/ provide appropriate support to promote research activities intended to provide solutions for the country's health problems and for improving health service delivery;

12/ expand health education through various appropriate means;

13/ ensure the proper execution of food, medicine and health care regulatory functions;

14/ lead the national social health insurance system and follow its implementation.

34. **The Ministry of Labour and Social Affairs**

The Ministry of Labour and Social Affairs shall have the powers and duties to:

1/ with a view to ensuring the maintenance of industrial peace:

a) supervise and ensure the proper enforcement of labour laws;

b) establish a system to maintain industrial peace and ensure its proper implementation;

c) encourage and support employers and workers to form organization and thereby exercise their rights of collective bargain;

d) encourage the practice of bipartite forums between workers and employers and tripartite forums involving the Government;

ሠ) የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ የሚያስ ችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበት የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፪/ በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችንና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደህንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

፫/ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማኀበራት ይመዘግባል፤

፭/ ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኀበራትንና የሕብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሠሪ ዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፤

፮/ ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶች የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን ተፈጻሚነት ያረጋግጣል፤

፯/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተመባበር መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በአሠሪና ሠራተኛ አስተዳደር ግንኙነት ዙሪያ ይዘረጋል፤

፰/ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

e) set a mechanism to minimize occurrence of labour disputes and establish efficient system for settlement of same;

2/ establish a system to prevent occupational accidents and occupational diseases; issue occupational health and safety standards and supervise their impleme ntation;

3/ establish national labour sector information system and realize its implementation;

4/ register employers' association and trade unions established at national level;

5/ register trade unions and collective agreements relating to Federal Public Enterprises situated in cities accountable to the Federal Government; carry out labour inspection services in such enterprises; provide conciliation services to amicably settle labour disputes arising between employers and employees;

6/ follow up and support the labour relation of enterprises situated in more than one Regional States and ensure the enforcement of labour laws;

7/ in cooperation with concerned bodies, establish a labour administration system around their labour relation that enables the proper transition of the informal economy to the formal economy;

8/ enhance the accessibility of efficient and equitable employment services;

፱/ ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

፲/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮ ጵያውያን የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን ይቆጣጠራል፤

፲፩/ አገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፪/ የአገሪቱን የሠው ኃይልና የሥራ ስምሪት እንዲሁም የሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፤

፲፫/ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የዜጎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው ዘዴዎችን በሚመለከት በተለይም፡-

ሀ) የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣

ለ) አረጋዊያን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ተሳትፎአቸው እንዲጎለብት፣

ሐ) የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከ ላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

## ፴፭. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የኢትዮጵያ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ፣ባህላዊ ቅርሶችና እሴቶች እንዲጠኑ እንዲጠበቁ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፤

9/ issue work permits to foreign nationals and, in cooperation with concerned bodies, supervise the compliance therewith;

10/ in cooperation with concerned bodies, regulate the Ethiopians overseas employment;

11/ establish and put into operation a national labour market information system;

12/ carry out studies on national manpower and employment as well as occupational classification;

13/ work in collaboration with the concerned bodies to strengthen the social protection system to improve and ensure the social and economic wellbeing of citizens and, in particular to:

a) enable persons with disabilities benefit from equal opportunities and full participation;

b) enable the elderly to get care and support and enhance their participation;

c) prevent social and economic problems and provide different services to segments of the society under difficult circumstances.

## 35. The Ministry of Culture and Tourism

The Ministry of Culture and Tourism shall have the powers and duties to:

1/ cause the study and preservation of history, cultural heritages and values of the nations, nationalities and peoples of Ethiopia and enable them to serve for scientific and technological purposes;

፪/ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎች እንዲጠኑና ሥነጽሑፎቻቸው እንዲዳ ብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፫/ የትርጉም አገልግሎትና የአስተርጓሚነት ሙያ ዕውቀት እንዲዳብርና እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ተግባሮችን ያከናውናል፣ ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

፬/ በባህል ተፅእኖ ሳቢያ ማኀበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፤ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፤

፭/ የባህል ዘርፉ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፮/ በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፯/ የዕደ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብና የሥነ-ጥበብ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፰/ በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፱/ የሀገሪቱ የፊልም ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤

፲/ የሀገሪቱን የቱሪዝም መስሕቦችና መልካም ገፅታ በዓለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤ የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

2/ cause study of the languages of the nations, nationalities and peoples of Ethiopia and advancement and promotion of their literatures;

3/ undertake activities related to advance ment and promotion of translation services and translation as a professional knowledge; assist and follow up standard usage of working language and translation services;

4/ undertake activities to bring about changes in those cultural attitudes, beliefs and practices hindering social progress;

5/ promote the contribution of culture to development;

6/ expand cultural institutions to institutionalize public participation in the development of culture;

7/ promote creativity in handicraft, artistic works and fine art;

8/ establish and enforce a working procedure for awarding and motivating those individuals and institutions with outstanding achievements in creative industry;

9/ create conducive environment for the development of the country's film industry and theatrical arts;

10/ promote widely the country's tourist attractions and its positive image on the world tourism market, and encourage domestic tourism;

፲፩/ የሀገሪቱ ቱሪስት መስሕቦች ተለይተው እንዲታውቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው ማኅበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቸል፤

፲፪/ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በአግባቡ መመራቱን ያረጋግጣል፤

፲፫/ የባህልና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

፲፬/ በቱሪዝም የሠመረ አገልግሎት እንዲኖር የቱሪስቶችም ደህንንት እንዲረጋገጥ የሚያስፈልገው የብዙ ወገኖች የሥራ ቅንጅት እውን እንዲሆን ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤

፲፭/ በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የባህልና የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

፲፮/ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፡፡

## ፴፮. <u>የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

፩/ የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

11/ ensure that the country's tourist attractions are identified, properly developed and organized, tourist facilities are expanded, and that local communities share the benefits derived from tourism;

12/ facilitate the studying and preservation of the country's natural heritages and the development and utilization of them as tourist attractions; ensure the proper management of wildlife conservation areas designated to be administered by the Federal Government;

13/ set and supervise the enforcement of standards for culture and tourist facilities;

14/ serve as a focal point for forums established to facilitate the coordination of the multi-sectoral efforts required for the provision of quality tourist services and for ensuring the well-being of tourists;

15/ build the capacity of the Culture and Tourism Sector through the provision of human resource training and consultancy supports;

16/ collect, compile and disseminate information on culture and tourism.

## 36. <u>The Ministry of Women and Children Affairs</u>

1/ The Ministry of Women and Children Affairs shall have the powers and duties to:

ሀ) የሴቶችና ሕፃናትን መብትና ጥቅሞች ማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ለ) የሴቶችንና የሕፃናትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

ሐ) ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ/ ሴቶች እንደፍላጎቶቻቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ አቅማቸውን ይገነባል፤

ሠ) በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የህጻናትን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

ረ) በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሰ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ሸ) ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

a) create awareness and movement on the question of women and children;

b) collect, compile and disseminate to all stakeholders information on the objective realities faced by women and children;

c) ensure that opportunities are created for women to actively participate in political, economic and social affairs of the country;

d) encourage and support women to be organized, based on their free will and needs, with a view to defending their rights and solving their problems; and build their capacity;

e) design strategies to follow up and evaluate the preparation of policies, legislations, development programs and projects by Federal Government organs to ensure that they give due considerations to women issues;

f) undertake studies to identify discriminatory practices affecting women, facilitate the creation of conditions for the elimination of such practices, and follow up their implementation;

g) device means for the proper application of women's right to affirmative action's guaranteed at the national level and follow up the implementation of same;

h) ensure that due attention is given to assign women for decision-making positions in various Government organs;

ቀ) የህፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ያስተባብራል፤

በ) ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት ይዋዋላል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ሴቶችንና ሕጻናትን በሚመለከት ለሴቶች፣

ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

i) coordinate all stakeholders to protect the rights and well-being of children;

j) conclude international treaties relating to women and children in accordance with law and, follow up the implementation of same and submit reports to the concerned bodies.

2/ The powers and duties given to the Women, Children and Youth Affairs by the provisions of other laws, currently in force, with respect to women and children are hereby given to the Ministry of Women and Children Affairs.

## ፴፯. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር

፩/ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) የወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

ለ) የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤

ሐ) ወጣቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ) ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸውና እንደችግሮቻቸውቸው ተደራጅው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ሁኔታዎችንያመቻቻል፤አቅማቸውንም ይገነባል፤

## 37. The Ministry of Youth and Sports

1/ The Ministry of Youth and Sports shall have the powers and duties to:

a) create awareness and movement on the question of the youth;

b) collect, compile and disseminate to all stakeholders information on the objective realities faced by the youth;

c) ensure that opportunities are created for the youth to actively participate in political, economic and social affairs of the country;

d) encourage and support the youth to be organized, based on their free will and needs, with a view to defending their rights and solving their problems; and build their capacity;

ሠ) በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ሕጎች፣የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

ረ) ህዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

ሰ) የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሸ) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

ቀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፤ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

በ) የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ወጣቶችን በሚመለከት ለሴቶች፣ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ስፖርትን በሚመለከት ለስፖርት ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

e) design strategies to follow up and evaluate the preparation of policies, legislations, development programs and projects by Federal Government organs to ensure that they give due considerations to issues of the youth;

f) enable the public to participate in and benefit from sports-for-all and traditional sports;

g) design and implement strategies for the establishment of sport education, training and research institutions to produce trained manpower and to improve competence;

h) promote the expansion of sports facilities and centers;

i) organize sports medical facilities in cooperation with the appropriate bodies, and adopt systems for controlling doping practices;

j) issue directives governing the establishment of sports associations; register and support associations operating at the federal level.

2/ The powers and duties given to the Women, Children and Youth Affairs by the provisions of other laws, currently in force, with respect to the youth, and to the Sports Commission, with respect to sports, are hereby given to the Ministry of Youth and Sports.

**፴፰. ስለሌሎች የፌደራል አስፈጻሚ አካላት**

፩/ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች የተደረጉት የተጠሪነት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የፌደራል መንግሥት ሌሎች አስፈጻሚ አካላት በተቋቋሙባቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

፪/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን፤

ለ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን፡፡

፫/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፤

ለ) የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

ሐ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ፡፡

፬/ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለፍትህ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፭/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፤

ሀ) ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፤

ለ) የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፤

ሐ) የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት፡፡

፮/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ይሆናል፡-

**38. Other Federal Executive Organs**

1/ Without prejudice to the amendments made under the provisions of the following sub-articles with regard to accountability, other Federal executive organs shall continue to function in accordance with the legislations establishing them.

2/ The following executive organs shall be accountable to the Prime Minister:

a) the Ethiopian Broadcasting Authority;

b) the Ethiopian Commodity Exchange Authority.

3/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs:

a) the Federal Police Commission;

b) the Federal Prisons Administration;

c) the Charities and Societies Agency.

4/ The Justice and Legal System Research Institute shall be accountable to the Ministry of Justice.

5/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Public Service and Human Resource Development:

a) the Civil Service University;

b) the Ethiopian Management Institute;

c) the Ethiopian Kaizen Institute.

6/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Finance and Economic Cooperation:

ሀ) የመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ፣

ለ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣

ሐ) የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ቦርድ፣

መ) የመንግሥት ግዥና የንብረት ማስወገድ አገልግሎት፡፡

፯/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ይሆናል፣

ሀ) የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣

ለ) የህብረት ሥራ ኤጀንሲ፣

ሐ) የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣

መ) የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ፣

ሠ) የኢትዮጵያ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ፣

ረ) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፡፡

፰/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

ለ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣

ሐ) ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት፣

መ) ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል፣

a) the Public Procurement Agency;

b) the Board of Trustee for Public Enterprises;

c) the Accounting and Auditing Board of Ethiopia;

d) the Public Procurement and Property Disposal Service.

7/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Agriculture and Natural Resources:

a) the Ethiopian Institute of Agricultural Research;

b) the Cooperatives Agency;

c) the Ethiopian Horticulture Development Agency;

d) the Strategic Food Reserve Agency;

e) the Ethiopian Agricultural Investment Land Administration Agency;

f) the Agricultural Transformation Agency.

8/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Livestock and Fisheries:

a) the Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority;

b) the National Veterinary Institute;

c) the National Institute for Control and Eradication of Tsetse Fly and Trypanosomosis;

d) the National Animal Health Research Center;

ሠ) የብሔራዊ ሰው ሠራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል፤

፱/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለኢን ዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፤

ለ) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፤

ሐ) የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

መ) የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱ ስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፤

ሠ) የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱ ስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፤

ረ) የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡፡

፲/ የሚከተለው ተቋም ተጠሪነት ለንግድ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

የኢትዮጵያ የንግድ ውድድር የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን።

፲፩/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለሥልጣን፤

ለ) የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት፡፡

፲፪/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ይሆናል፡-

e) the National Animal Artificial Insemination Center;

9/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Industry:

a) the Textile Industry Development Institute;

b) the Leather Industry Development Institute;

c) the Metals Industry Development Institute;

d) the Food, Beverage and Pharmaceutical Industry Development Institute;

e) the Chemical and Construction Inputs Industry Development Institute;

f) the Ethiopian Meat and Dairy Industry Development Institute.

10/ The following organ shall be accountable to the Ministry of Trade:

the Ethiopian Trade Competition and Consumers Protection Authority;

11/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Science and Technology:

a) the Ethiopian Radiation Protection Authority;

b) the Ethiopian Intellectual Property Office.

12/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Transport:

ሀ) የፌደራል ትንስፖርት ባለሥልጣን፣

ለ) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን፣

ሐ) የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን፣

መ) የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት፡፡

፲፫/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ፣

ለ) የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረቶች ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፡፡

፲፬/ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፭/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለውሃ፣መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን፣

ለ) የዓባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን፣

ሐ) የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን፣

መ) ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ፣

ሠ) የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት፣

ረ) የኢትዮጵያ ኤነርጂ ባለሥልጣን

ሰ) የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፡፡

፲፮/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ይሆናል፡-

a) the Federal Transport Authority;

b) the Ethiopian Civil Aviation Authority;

c) the Maritime Affairs Authority;

d) the Road Fund Office.

13/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Urban Development and Housing:

a) the Agency for Government Houses;

b) the Federal Urban Real Property Registration and Information Agency.

14/ The Ethiopian Construction Project Management Institute shall be account able to the Ministry of Construction.

15/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Water, Irrigation and Electricity:

a) the Awash Basin Authority;

b) the Abay Basin Authority;

c) the Rift Valley Lakes Basin Authority;

d) the National Meteorology Agency;

e) the Water Resources Development Fund Office;

f) the Ethiopian Energy Authority;

g) the Ethiopian Water Technology Institute.

16/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas:

ሀ) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ፤

ለ) የአዶላ ወርቅ ልማት ድርጅት።

፲፯/ የብዝሐ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለአካባቢ፣ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፰/ የሚከተሉት ተቋማት ተጠሪነት ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ይሆናል፦

ሀ) የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት፤

ለ) የስኳር ኮርፖሬሽን፤

ሐ) የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን፤

መ) ኬሚካል ኮርፖሬሽን፤

ሠ) የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

፲፱/ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶች ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል።

፳/ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፳፩/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል፡-

ሀ) የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፤

ለ) የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ፤

ሐ) ብሔራዊ ቲያትር፤

መ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል፡፡

a) the Ethiopian Geological Survey;

b) the Adola Gold Mining Enterprise.

17/ The Institute of Biodiversity Conservation shall be accountable to the Ministry of Environment, Forest and Climate Change.

18/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Public Enterprises:

a) the Ethiopian Shipping and Logistics Service Enterprise;

b) the Sugar Corporation;

c) the Ethiopian Railway Corporation;

d) the Chemical Coporation;

e) the Berhanena Selam Printing Enterprise.

19/ The Educational Materials Production and Distribution Enterprise shall be accountable to the Ministry of Education.

20/ The HIV/AIDS Prevention and Control Office shall be accountable to the Ministry of Health.

21/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Culture and Tourism:

a) the Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage;

b) the National Archives and Library Agency;

c) the National Theatre;

d) the Ethiopian National Cultural Center.

**፴፱. የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለ ማደራጀት**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ፣ ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል በማድረግ፣ ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ በማድረግ ወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም በማድረግ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና የማደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፵. የተሻሩ ሕጎች**

፩/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

ሀ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (እንደተሻሻለ)፤

ለ) የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፪/፪ሺ፫ ፤

ሐ) የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፪/፲፱፻፺፮ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድን ከሚመለከተው አንቀጽ ፲፫ (በአዋጅ ቁጥር ፯፻፴/፪ሺ፬ እንደተሻሻለው) በስተቀር፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**39. Re-organization of Federal Executive Organs**

The Council of Ministers is hereby empowered, where it finds it necessary, to reorganize the Federal executive organs by issuing regulations for the closure, merger or division of an existing executive organ or for change of its accountability or mandates or for the establishment of a new one.

**PART FOUR**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**40. Repeal**

1/ The following legislations are hereby repealed:

a) the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended);

b) the Sport Commission Establishment Proclamation No. 692/2010;

c) the Privatization and Public Enterprises Supervising Agency Establishment Proclamation No. 412/2004, except its Article 13 (as amended by Proclamation No. 730/2012) which governs the Industry Development Fund.

2/ No laws, regulations, directives or practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, have force or effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

## ፵፩. መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

፩/ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፪/ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፫/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ማኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፬/ የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ዘርፍን ከሚመለከቱት በስተቀር የግብርና ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፭/ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የግብርና ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፮/ የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍን የሚመለከቱ የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፯/ የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍን ከሚመለከቱት በስተቀር የከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

## 41. Transfer of Rights and Obligations

1/ The rights and obligations of the Ministry of Federal Affairs are hereby transferred to the Ministry of Federal and Pastoralist Development Affairs.

2/ The rights and obligations of the Ministry of Civil Service, are hereby transferred to the Ministry of Public Service and Human Resource Development.

3/ The rights and obligations of the Ministry of Finance and Economic Development are hereby transferred to the Ministry of Finance and Economic Cooperation.

4/ The rights and obligations of the Ministry of Agriculture, other than those relating to livestock and fish resources development sector, are hereby transferred to the Ministry of Agriculture and Natural Resources.

5/ The rights and obligations of the Ministry of Agriculture, relating to livestock and fish resources development sector, are hereby transferred to the Ministry of Livestock and Fisheries.

6/ The rights and obligations of the Ministry of Urban Development, Housing and Construction, relating to urban development and housing sector, are hereby transferred to the Ministry of Urban Development and Housing.

7/ The rights and obligations of the Ministry of Urban Development, Housing and Construction, other than those relating to urban development and housing sector, are hereby transferred to the Ministry of Construction.

፰/ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለውሃ፣መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፱/ የማዕድን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፲/ የአካባቢና የደን ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፲፩/ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

፲፪/ የወጣቶች ጉዳይን ከሚመለከቱት በስተቀር የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፲፫/ የስፖርት ኮሚሽን እና የወጣቶች ጉዳይን የሚመለከቱት የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

8/ The rights and obligations of the Ministry of Water, Irrigation and Energy are hereby transferred to the Ministry of Water, Irrigation and Electricity.

9/ The rights and obligations of the Ministry of Mines are hereby transferred to the Ministry of Mines, Petroleum and Natural Gas.

10/ The rights and obligations of the Ministry of Environment and Forest are hereby transferred to the Ministry of Environment, Forest and Climate Change.

11/ The rights and obligations of the Privatization and Public Enterprises Supervising Agency are hereby transferred to the Ministry of Public Enterprises.

12/ The rights and obligations of the Ministry of Women, Children and Youth Affairs, other than those relating to youth affairs, are hereby transferred to the Ministry of Women and Children Affairs.

13/ The rights and obligations of the Ministry of Women, Children and Youth Affairs, those relating to youth affairs, and the rights and obligations of the Sport Commission are hereby transferred to the Ministry of Youth and Sports.

**፵፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**42. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on this 9th day of December, 2015.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of December, 2015.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**